# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 101 ሚያዝያ 14 2002 ዓ.ም


ምርጫን እንደመሰለያ መሳሪያ የሚጠቀመው ወያኔ በድህረ ምርጫ 97 በህዝባችን ላይ የፈጸመው አይነት ፋሽስታዊ ጭፍጨፋ እንዳይደገም ከተፈለገ፣ ነጻ እና ገለልተኛ የሆነ የምርጫ አስፈጻሚ አካላት፤ ለሁሉም እኩል የሚያገለግል የሚዲያ አገልግሎት፤ ታማኝነታቸው ለህገመንግሥቱ ብቻ የሆነና ከፖለቲካ ወገናዊነት የጸዱ የፖሊስ፤ የመከላኪያና የደህንነት ተቋማት መመስረት ይኖርበታል።

ለወያኔ እድሜ መራዘሚያ ህጋዊና ሞራላዊ መሰረት እንዲያስገኝ ታስቦ በሚካሄድ ምርጫ መሳተፍ ለህዝባችን የሚያስገኘው ፋይዳ አይኖርም!!!

## ዘረኛው አምባገነን መለስ ዜናዊ ከመጪው ወር የምርጫ ተውኔት በኋላ አንዳንድ ባለስልጣናቱን ከስራ ሊያባርር እንዳቀደ ምንጮች ገለጹ

አምባገነን መለስ ዜናዊ ከመጪው ግንቦት የምርጫ ተውኔት በኋላ በአንዳንድ ባለስልጣናቱ ላይ እርምጃ ሊወስድ እንደሚችል ምንጮቻችን ገለጹ። ከነዚህም ውስጥ የገንዘብ እና ልማት ሚኒስቴር ሃላፊ ሱፊያን አህመድ አንዱ እንደሆነ በመስሪያ ቤቱ የሚገኙ ምንጮች ለግንቦት 7 ዘጋቢ ነግረዋል።

እንደ ምንጮቹ ገለፃ፥ ጉዳዩ የሚመለከተው ከውጭ እርዳታ በተገኘ ገንዘብ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ውስጥ ሲሰራ የነበረን ፕሮጀክት ሲሆን፤ ሱፊያን አህመድ ለፕሮጀክቱ ሊውል የሚገባውን ገንዘብ በመመዝበር ተካፍሏል የሚል መረጃ ከጅማሬው ለአምባገነን መለስ ቢደርሰውም የምርጫ ተውኔቱ እስኪጠናቀቅ ድረስ እርምጃ ላለመውሰድ መወሰኑን ምንጮቹ ገልጸዋል።

አምባገነን መለስ ዜናዊ ከግንቦት በኋላ ብዙ ባለስልጣናቱን በጡረታ ስም የማስወገድ እቅድ እንዳለው አገዛዙ መግለጹ ይታወሳል። ይህ የሱፊያን አህመድ ጉዳይ ደግሞ አንዳንዶቹ ባለስልጣናት እንደ ከዚህ በፊቱ በሙስና እየተከሰሱ ለመለስ የፖለቲካ ፍጆታ ሲባል ሊባረሩ እንደሚችሉ ጠቋሚ ነው ሲሉ በጉዳዩ ላይ ያነጋገርናቸው የፖለቲካ ተንታኝ ገልጸዋል።

አምባገነን መለስ ዜናዊ እና ባለቤቱ በከፍተኛ ሙስና ውስጥ ተዘፍቀው እንደሚገኙ በተለያዩ ጊዜያት መዘገባችን ይታወሳል። በቅርቡ ከግንቦት 7 ድምጽ ጋር ቃለ-መጠይቅ ያደረጉት እና ጀኖሳይድ ዋች ተብሎ የሚታወቀው የሰብአዊ መብት ተከራካሪ ድርጅት ፕሬዘደንት የሆኑት ዶ/ር ግሬገሪ ስታንተን በተለያዩ አለም አቀፍ ባንኮች የሚገኙ ምንጮችን ጠይቀው መለስ ዜናዊ ቢሊዬነር መሆኑን ለማወቅ መቻላቸውን መግለጻቸው ይታወቃል።

## ከወያኔ ጋር በጥቅምና በሙስና የተሳሰሩ ነጋዴዎች ጨቋኙ አገዛዝ በስልጣን ላይ እንዲቆይ እየሰሩ መሆኑ ታወቀ

በወያኔ ድጋፍ የከበሩና ከአገዛዙ ጋር ያላቸውን የቅርብ ግንኙነት በመጠቀም በየንግድ ዘርፎቻቸው እራሳቸውን ከውድድር ነጻ በማድረግ የሚንቀሳቀሱ ነጋዴዎች፣ ጨቋኙ አገዛዝ ስልጣን ይዞ እንዲቆይ እንደሚፈልጉና እንደሚረዱም ታውቋል።

አዲስ ፎርቹን የተባለው የእንግሊዝኛ ጋዜጣ ባለፈው እሁድ ባቀረበው ዘገባ፥ የኢትዮጵያ አበባ አምራቾች ማህበር ፕሬዚደንት በሆኑት አቶ ጸጋዬ አበበ እና ሌሎች ነጋዴዎች አስተባባሪነት በአዲስ አበባ ኮንቬንሽን ማእከል በተደረገ ስብሰባ 20 ሚሊዮን ብር ለወያኔ መሰብሰቡን ገልጿል። ብዙ ነጋዴዎች ከአምባገነናዊው አገዛዝ ሊደርስባቸው የሚችለውን ግፍ በመፍራት የሚተባበሩ እንደሆነ ቢታወቅም፤ እንደ አቶ ጸጋዬ አበበ ያሉ ጥቂት ግለሰቦች ግን በራስ ተነሳሽነት ለወያኔ ድጋፍ ከሚያሰባስበው የነጋዴዎች ኮሚቴ ውስጥ መግባታቸውን ለግንቦት 7 የደረሰ መረጃ አሳይቷል። **(ወደ ገጽ 2 ዞሯል)**

## የኮንዶሚኒየም ቤቶች ተጠቃሚ ለመሆን የወያኔ አባልነት እንደሚያስፈልግ ታወቀ

በአዲስ አበባ ከተማ የኮንዶሚኒየም ቤቶች ተጠቃሚ ለመሆን እጣ ወጥቶላቸው የነበሩ ነዋሪዎች በእጣቸው መሰረት ቤቶቹ ሊሰጡዋቸው ባለመቻላቸው እያማረሩ መሆኑ ታውቋል።

4000 የሚሆኑ ቤቶች እጣ ለወጣላቸው እድለኞች መሰጠት ሲገባቸው እስካሁን አለመሰጠታቸውን፤ በሌላ በኩል ግን የገዢው ፓርቲ አባላት ለሆኑት እየተሰጡ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል። የአዲስ አበባው ዘጋቢያችን አጠናቅሮ የላከልን ዜና እንደሚገልጸው የኮንዶሚኒየም ቤት እጣ ደርሷቸው ቤቶቹን ግን ያልተረከቡት ነዋሪዎች ቤቶቹ ለምን እንደማይሰጡዋቸው ጥያቄ ሲያቀርቡ ምላሽ አለማግኘታቸውን፤ ነገር ግን የአምባገነኑ አገዛዝ ካድሬዎች የወያኔ አባል እንዲሆኑ እንደሚገተጉቷቸው ለማወቅ ተችሏል።

ካድሬዎቹ፥ ቤቶቹ የተዘጋጁት በማህበረሰቡ ውስጥ ለወያኔ ቅስቀሳን ለማድረግ ፈቃደኛ ለሆኑ አዳዲስ የፓርቲ አባላት ነው በማለት ለእጣ አሸናፊዎቹ መናገራቸውም ታውቋል። በአሁኑ ሰአት በኢትዮጵያ ውስጥ ከገጠር እስከ ከተማ ያሉ ዜጎች ብዙ የመንግስት አገልግሎቶችን የፓርቲ አባል ካልሆኑ ለማግኘት እንደማይችሉ ሲዘገብ ቆይቷል።

## የግንቦት 7 ድምጽ ሬድዮ በአራት አዳዲስ ሞገዶች ላይ ስርጭቱን ማስተላለፍ መጀመሩን አስታወቀ

የግንቦት 7 ድምጽ ሬድዮ ወያኔ በአገር ውስጥ ስርጭቱ ላይ የሚያደርገውን ጃሚንግ ወይም አፈና ለመቋቋም ሲል የስርጭት ሞገዶቹን በእጥፍ በመጨመር፤ ስርጭቱን በአራት አዳዲስ ሞገዶች ላይ እንደሚያስተላልፍ አስታውቋል።

ከሚያዚያ 12 ቀን 2002 አመተ ምህረት ጀምሮም፥ በ41 ሜትር ባንድ ላይ በ7185፣ በ7140 ወይም በ7175 ኪሎ ኸርዞች ላይ፤ እንዲሁም በ49 ሜትር ባንድ በ6100 ኪሎ ኸርዝ፤ ላይ የግንቦት 7 ድምጽ ሬድዮ ስርጭት እንደሚተላለፍ ታውቋል።

የስርጭት ሞገዶቹን ቁጥር ከማሳደግ በተጨማሪም፥ ከዚህ ቀደም ዘወትር ማክሰኞ፣ ሐሙስና ቅዳሜ ምሽት ላይ ብቻ ይተላለፉ የነበሩት ዝግጅቶች፤ ከዛሬ ጀምሮ በነዚሁ ቀናቶች ጠዋት ላይም እንደሚተላለፉ ለማወቅ ተችሏል። በዚህ መሰረት፥ የግንቦት 7 ድምጽ ሬድዮ ዝግጅቶች፣ ዘወትር ማክሰኞ፣ ሐሙስ እና ቅዳሜ ከጠዋቱ 3 ሰዓት እስከ 3:30፤ እንዲሁም ከምሽቱ 2 ሰዓት እስከ 2:30 እንደሚተላለፉ ታውቋል።

የግንቦት 7 ድምጽ የሬድዮ ዝግጅት ክፍል ይህንን ዜና የሰሙ ወገኖች ለሌሎችም በማስተላለፍ እንዲተባበሩ የአክብሮት ጥሪውን አቅርቧል።

## ያለፈው የፓርላማ ስብሰባ፥ የዘረኛው አምባገነን መለስ ዜናዊ ፍርሃትና ጭንቀት ከገደብ ማለፉን አሳይቷል ተባለ

ማክሰኞ፣ ሚያዚያ 5 ቀን በተካሄደው የፓርላማ ምክር ቤት ተብየው ስብሰባ አምባገነኑ መለስ ዜናዊ የተናገራቸው አጸያፊ ቃላትና የማስፈራሪያ ዛቻዎች መለስ ምን ያህል በፍርሃትና በጭንቀት አዘቅት ውስጥ ተቀብሮ እንደሚገኝ በግልጽ ያሳዩ መሆናቸውን የግንቦት ሰባት ዜና ዘጋቢ ተዘዋውሮ ያነጋገራቸው የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች ገለጹ።

አብዛኞቹ አስተያየት ሰጪዎች እንደተናገሩት የዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ቁንጮ አምባገነን መለስ በስብሰባው ላይ በተለይም የተቃዋሚ ፓርቲ ተወካዮችን ተራ የጋጠወጥ ስድብ መሳደቡና ማለቂያ የሌለው የማስፈራሪያ ዛቻው ከአንድ ጠቅላይ ሚንስትር በፍጹም የማይጠበቅ ከመሆኑም በላይ የኢትዮጵያዊንን ባህል ያልጠበቀ አሳፋሪ ተግባር እንደሆነም ገልጸዋል።

አንድ አስተያየት ሰጪ፥ አገዛዙ ምንም እንኳ ምርጫውን ለመስረቅ የሚያስችለውን ቅድመ ዝግጅት ሁሉ ቢያደርግም፤ በህዝብ የተጠላ እንደሆነ ስለሚያውቅ በስርቆት ውጥኑ እንኳ ሊተማመን አልቻለም ብለዋል። የመለስን ዛቻ በሚመለከት የተናገሩት ሌላው ግለሰብ ደግሞ፥ **(ወደ ገጽ 2 ዞሯል)**

## አርሶ አደሮች ወያኔ የግብርና ልማት ሰራተኞችን በመጠቀም በሚያደርገው የምረጡኝ ግፊት ላይ ምሬታቸውን ገለጹ

ሰሞኑን የግንቦት 7 ዘጋቢ ያናገራቸው ኢትዮጵያውያን አርሶ አደሮች የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ህገ-ወጥ በሆነ መንገድ የግብርና ልማት ሰራተኞችን በማዝመት የሚያደርግባቸው የምረጡኝ ግፊት እንዳማረራቸው ገልጸዋል።

መንግስት ሰራተኞች በመጪው ግንቦት ወር ሊካሄድ በታቀደው የምርጫ ተውኔት የፓርቲ አባል በመሆን እና አገዛዙን በመምረጥ እንዲደግፉ በርካታ ህገ-ወጥ ጫናዎች ሲደረጉባቸው እንደቆዩ መዘገባችን ይታወሳል። በዚህ ሳምንት እንደ ደረሰን ዘገባ ደግሞ፥ ከራሳቸው አልፈው በማህበረሰቡ ውስጥ በመዘዋወር ወያኔን ምረጡ በሚል ጫና እንዲያደርጉ እየተገደዱ መሆኑ ታውቋል።

በዚህም መሰረት የገጠር የግብርና ልማት ሰራተኞች በአርሶ አደሮች ቤቶች እየተዘዋወሩ ለወያኔ የምረጡኝ ዘመቻ ሲያካሄዱ መቆየታቸውን ዘጋቢያችን በላከው መረጃ አስረድቷል። በጉዳዩ መሰላቸታቸውን ለዘጋቢያችን የገለጹ አርሶ አደሮች፥ "ነፃ ምርጫ ያለ ይመስል ለምን ያስጨንቁናል፤ ሰራተኞቹስ ቢሆኑ የፖለቲካ ስራ ትተው በግብርና ስራችን ለምን አይረዱንም?" የሚሉ ስሞታዎችን አሰምተዋል።

ዘጋቢያችን ባደረጋቸው ተጨማሪ አሰሳዎች፣ በከተማዎችም ተመሳሳይ ጫናዎች በመንግስት ሰራተኞች ላይ እየተደረጉ እንደሆነ ተረድቷል። አንዳንድ ምንጮችን አናግሮ ባገኘው መረጃ መሰረትም፥ የአገዛዙ እቅድ አሉኝ የሚላቸው 4 ሚሊዮን አባላት እያንዳንዳቸው ቢያንስ አምስት ሰዎችን እንዲያሳምኑ እና ከሃያ ሚሊዮን በላይ መራጮችን ለማግኘት ነው። ገዢው ፓርቲ ስልጣን ከተቆጣጠረበት ጊዜ ጀምሮ ህገ-ወጥ በሆነ አክኋን ከህዝብ በግብር መልክ የተሰበሰበን የመንግስት ገንዘብ እንደሚጠቀም የሚታወቅ ሲሆን፤ የመንግስት መስሪያ ቤቶችን ሰራተኞችና ንብረት መጠቀም ከጥቂቶቹ የሚጠቀሱ ናቸው።

**(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)**

## በሙስና የነቀዘው የወያኔ ሥርዓት በፍጥነት መወገድ አለበት፤ ይህን ማድረግ ደግሞ ይቻላል!!!

የዘረፋ መሠረቶችን በማስፋት እና አዳዲስ የአዘራረፍ "ጥበቦችን" በመፈልሰፍ ረገድ የወያኔን ያህል የተሳካለት የማፍያ ድርጅት ማግኘት አይቻልም። ወያኔ ለዓለም ያስተዋወቃቸው የዘረፋ ዓይነቶችና ስልቶችን ለመዘርዘር ሰፊ ጥናት የሚጠይቅ ቢሆንም ለጊዜው በአራት ዋና ዋና ክፍሎች መድበን ማየት እንችላለን፡- 1ኛ/ ግልጽ ዘረፋ፣ 2ኛ/ ከፊል ግልጽ ዘረፋ፣ 3ኛ/ ድብቅ ዘረፋ፣ እና 4ኛ/ ይሉኝታ ቢስ ዘረፋ።

"ግልጽ ዘረፋ" ብለን የሰየምነው በእብሪት የሚፈፀሙ ገሃድ ዘረፋዎችን ነው። የገጠርና የከተማ መሬት እና ከውጭ አገራት የሚገኝ እርዳታ ሙሉ በሙሉ በወያኔ ቁጥጥሩ ሥር መሆኑ የግልጽ ዘረፋ በርን ወለል አድርጎ ከፍቷል። መሬትና የእርዳታ ገንዘብ በማደል ወያኔ የሚፈልጋቸውን ሰዎች በአንድ ቀን ሚሊየነር ማድረግ ይችላል።

የንግድና የሥራ ፈቃዶች፣የገበያ መረጃዎች፣ የሥራ ኮንትራቶች፣ ግብርና ታክሶች በወያኔ የእለት ከእለት ቁጥጥር ውስጥ መሆናቸው በከፊል ገሃድ በከፊል ደግሞ ድብቅ የሆኑ ዘረፋዎችን ለማካሄድ አመቺ ሁኔታዎች ፈጥረዋል። ወያኔ በእነዚህ በከፊል የተሸፈኑ ዘረፋዎች ራሱንና ወዳጆቹን ለመጥቀም እና ተቃዋሚዎቹን ለማጥቃት ይጠቀምባቸዋል።

የዋጋ ንረት እና የባንክ ብድር ደግሞ የድብቅ ዘረፋ ምሳሌዎች ናቸው። ወያኔ የዋጋ ንረትን በድብቅ የሃብት ማስተላለፊያ መሳሪያነት ይጠቀማል። አነስተኛና መካከለኛ ገቢ ያለው ኢትዮጵያዊ ለፍቶ አዳሪ በባንክ የሚያስቀምጠውን ትናንሽ ገንዘብ እያጠራቀመ ለቱጃር ወያኔ ነጋዴዎች በብድር መልክ ከዋጋ ንረቱ ምጣኔ ባነሰ ወለድ ያበድራቸዋል። አንዳች የረባ ነገር ሳይሰራ ገንዘብ በመበደር ብቻ መክበር የዘመኑ የወያኔ ድብቅ ዘረፋ ስልት ነው።

በመጨረሻም በገቢ ማሰባሰቢያ ዘመቻዎች ቴሌ ቶኖች እና መሰል ዝግጅቶች አማካይነት ገንዘብ ማግበስበስን "ይሉኝታ ቢስ" ዘረፋ ብለን ሰይመነዋል፤ የዛሬ ትኩረታችንም በዚህ ላይ ነው።

የወያኔን የሃብት ጥማት፤ የምኞትና የእዩልኝ ፍላጎቶችን ማርካት በጭራሽ አይቻልም። ለዚህም ነው በግራም በቀኝም፤ በግልጽም በድብቅም እየዘረፈ ቢሆንም እንኳን ስለማይበቃው በሰበብ አስባቡ መዋጮ እየሰበሰበ ያለው። ወያኔ "የልማት ገቢ ማሰባሰቢያ" ብሎ በሚጠራቸውና ሂሳባቸው ተመርምሮ በማያውቁ የዘረፋ ፕሮግራሞቹ አማካይነት ያካበተውን ሃብት ትተን ለራሱ ለወያኔ ድርጅት ማጠናከሪያነት የተዋጣውን ብቻ እንኳን ብናሰላ ለማመን የሚያስቸግር ነው።

ከበርካታ የወያኔ ማጠናከሪያ መዋጮዎች ውስጥ ለአብነት ሁለቱን ብቻ እናንሳ። ወያኔ በመሃል አራት ኪሎ - ጽህፈት ቤት፤ ሰንዳፋ ደግሞ የካድሬዎች ማሰልጠኛ ማሠራት ስላማረው በ2000 ዓ.ም. 130 ሚሊዮን ብር እንዲዋጣለት አዞ ከፊሉ በደስታ ከፊሉ ደግሞ በፍርሃት አዋጥቶለታል። አሁን ደግሞ ለ2002 ምርጫ ማስፈፀሚያ 20 ሚሊዮን ብር በዚያው መንገድ ተዋጥቶለታል። ሁለቱን ለአብነት የጠራናቸው ምሳሌዎችን ብቻ እንኳን ብናይ ከገንዘቦቹ በተጨማሪ ሌሎች በርካታ አስገራሚ ነገሮችን በውስጣቸው ይዘዋል።

1. ተቃዋሚ ፓርቲዎች የኪራይ ቤት ማግኘት ተቸግረው ባሉበት ወቅት ወያኔ እዚያው ፓርላማው አጠገብ ባለ ግዙፍ ህንፃ ውስጥ እየተቀማጠለ ነው። ህንፃውን በጽ/ቤትነት ይዞታል። ለ18 ዓመታት የዚህን ህንፃ ኪራይ ከፍሎ አያውቅም። አሁን ደግሞ ይግረማችሁ ብሎ ሌላ አዲስ ህንፃ አማረው። ለዚህም ማሰሪያ አዋጡ ተብሎ የውዴታ የሚመስል ሆኖም ግን ግዴታ የሆነ ወረቀት በተለይ ለነጋዴው ህብረተሰብ ዞረለት። አንዳንዱ እየተደሰተ፤ ሌላው እየከፋው አዋጣ። ለመሆኑ ወያኔ አዲስ ህንፃ ለምን ፈለገ? በህንፃ ገዝፎ ለመታየት? ለጉራ?
2. ለካድሬ ማሰልጠኛነት ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ አለ። ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ ቀድሞውኑ የተቋቋመው ለዚሁ ተግባር ነው። አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲን ጨምሮ የሃገሪቷ ዩኒቨርስቲዎች በተለይም የማኅበራዊ ሳይንስ ትምህርት ፋካልቲዎቻቸው ወደ ካድሬ ማሰልጠኛነት ወርደዋል። ታድያ ይኸ ሁሉ የካድሬ ማሰልጠኛ እጁ ውስጥ እያለ ተጨማሪ የካድሬ ማሰልጠኛ ሰንዳፋ ውስጥ መገንባት ለምን አስፈለገ? ለስም? ለታይታ? ለጉራ?
3. ለምርጫ 2002 የተዋጣው 20 ሚሊዮንስ ለደስደስ ግብዣ ካልሆነ በስተቀር ምን ሊሰራበት ነው? ውጤቱ አስቀድሞ ለታወቀ ምርጫ ወጪ ማውጣት ለምን ያስፈልጋል?

ወያኔ በሰላማዊ መንገድ እንፎካከራለን የሚሉ ፓርቲዎችን የገቢ ምንጮችን ዘጋግቷል። ለተቃዋሚ ፓርቲዎች እርዳታ ያደረጉ ነጋዴዎች በተለያዩ ስውርና ግልጽ መንገዶች ተቀጥተዋል። ተቃሚዎችን የሚረዱ ሰዎች በፍርሃት ምክንያት የእርዳታ እጃቸውን እንዲሰበስቡ አለያም አድኖ ለመያዝ እንዲመቸው የለጋሾች ስምና አድራሻ ተመዝግቦ እንዲያዝ የሚያስገድድ ህግ አወጣ። በአንፃሩ ወያኔን የደገፉ ነጋዴዎች ደግሞ በየእለቱ ሲያድጉና ሲመነድጉ እየታየ ነው። ወያኔን በገንዘብ መደገፍ ራሱን የቻለ አትራፊ ንግድ በመሆኑ ውድድሩ ተጧጡፏል። ይህ ነው የስብሃት ነጋ ካፒታሊዝም!

ወያኔ አንዳችም የገንዘብ ችግር ባይኖርበትም በገንዘብ "እየደገፉት" ያሉ ሁለት ዓይነት ነጋዴዎች አሉ።

ሀ) አንደኛው የነጋዴዎች ቡድን የተገነባው እጣ ፈንታቸው ከወያኔ ጋር በተቆራኙ አባላት ነው። ይህ የነጋዴዎች ቡድን ራሱ የወያኔ ተቀጥላ ነው። የዚህ ቡድን ስኬት በወያኔ መኖር የተመሠረተ ነውና ገንዘቡን ብቻ ሳይሆን ደሙን ቢሰጥ ሊገርመን አይገባም። ወያኔ ያለቦታቸው የሚጠቀምባቸው "ጥገኛ" እና "ኪራይ ሰብሳቢ" የሚባሉት ቃላት ትክክለኛ ቦታቸው እዚህ ነው። የእነዚህ ነጋዴዎች "የስኬት እድሜ" የወያኔ እድሜን ያህል ያጠረ ነው። የዚህ ቡድን አባላት ከውንብድና ጋር በመሻረክ ያጋበሱትን ሃብት ከወያኔም በኋላ አብሯቸው እንደሚቆም ማንም ቃል ሊገባላቸው አይችልም።

ለ) ሁለተኛው ቡድን አብዛኛውን የወያኔ ደጋፊ የንግድ ማኅረበረሰብን ያቀፈ ነው። ይህ የማኅበረሰብ ክፍል ወያኔ እያደረሰብን ያለውን ጥፋት በሚገባ ይገነዘባል። ሆኖም ግን ራሱን ከወያኔ ጥቃት ለመከላከል ወዳጅ መስሎ መታየት ይፈልጋል። የዚህ ቡድን አባላት ንግዳቸውን ከወያኔ አፈና ለመከላከል እና ከመንግሥት ሊያገኙት የሚገባው አገልግሎት እንዳይቋረጥባቸው በመፍራት በመዋጮ ይሳተፋሉ። ይህ "የወይን ለመኖር" አንዱ ገጽታ ነው። ለመነገድ ሲባል ወያኔ መሆን ማለት ነው።

ወያኔ ስግብግብ ነው። እስከመቼውም ቢሆን ለንዋይ ያለውን ጥማት፤ የጉራና የእዩልኝ ፍላጎቶቹን ማርካት አይችልም። ወያኔ እንደተራበ ያደገ፤ እንደተራበ የሚጠፋ ድርጅት ነው። እስኪጠፋ ግን የሚያባክነው የሃገር ሃብት በጣም አሳሳቢ ነው።

በግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና ዲሞክራሲ ንቅናቄ እምነት መፍትሄው ግልጽ ነው። ይህ እስከ አጥንቱ ድረስ በሙስና የነቀዘ ሥርዓት በፍጥነት መወገድ ይኖርበታል፤ በምትኩም ፍትህ የሰፈነባት እና የዜጎቿ ነፃነት የተከበረባት ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ መገንባት አለባት። ይህን ማድረግ ደግሞ ይቻላል!!!

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

## ያለፈው የፓርላማ ስብሰባ፥ የዘረኛው አምባገነን . . . ከገጽ 1 የዞረ

አምባገነኑ ከዚህ ቀደም በተቃዋሚ ፓርቲዎች መሪዎች ላይ ከምርጫ በኋላ እርምጃ እንደሚወስድ መዛቱን አስታወሰው፤ በዚህኛው የፓርላማ ስብሰባ ላይ "እሳት ለኩሶ እንደቀድሞው በህጻናት ደም መጫወት አይኖርም" ማለቱ ብዙ እንድምታ አለው ብለዋል። በአንድ በኩል መለስ ዜጎችን በጭካኔ ስለመጨፍጨፉ በአደባባይ ለመጀመሪያ ጊዜ ያመነበት ሲሆን፤ በሌላ ጎኑ ደግሞ በዚህኛውም ምርጫ የንጹሃንን ደም አፍስሶ የተቃዋሚ ፓርቲዎችን የመወንጀል እቅድ እንዳለው እና ህዝቡም ተቃዋሚዎችም ከዚህ ምርጫ ፍትህን ቢጠብቁ፣ ሊደርስባቸው ስለሚችለው ቅጣት ማስጠንቀቂያ ነው ብለዋል።

አምባገነን መለስ በዚሁ ስብሰባ በምክር ቤቱ ውስጥ ያሉ አንዳንድ ተቃዋሚዎች የጥፋት ሃይል ከሚላቸው ሻእቢያና ኦነግ ጋር ሰርተዋል ሲልም ወንጅሏል። ይህም የተቃዋሚ መሪዎችን በሃሰት ወንጀሎች ለመክሰስ እና ለማሰር የሚያደርገው ዝግጅት አካል ነው ሲሉ በጉዳዩ ላይ አስተያየት የሰጡን ዜጎች ተናግረዋል።

## ከወያኔ ጋር በጥቅምና በሙስና የተሳሰሩ ነጋዴዎች . . . ከገጽ 1 የዞረ

እንደደረሰን መረጃ መሰረት፥ አቶ ጸጋዬ አበበ በአበባ አምራችነት በአጭር ጊዜ ውስጥ ሃብት ለማካበት የቻለ ሲሆን፤ የአበባ አምራቾች ማህበር ፕሬዚደንት ለመሆን የበቃውም በአገዛዙ ምርቃት መሆኑ ታውቋል። ቀደም ብሎ በተለያዩ የመረጃ አውታሮች አበባ አምራቾች ከመንግስት ባንኮች ልዩ የብድር ድጋፍ እንደሚሰጣቸው እና አቶ ጸጋዬ የሚመሩት የአምራቾች ማህበርም ብድሩን መክፈል አቅቶት እንደነበር መዘገቡ ይታወሳል።

የአበባ እርሻ ሰራተኞች በደሞዝ ክፍያ እና የጤና ጥበቃ ማነስ እንደሚጨቆኑና፤ ይህንን ጉዳይም ለመቅረፍ የተንቀሳቀሱን አንድ አበባ አምራች፣ አቶ ጸጋዬ ከአገዛዙ ጋር ያለውን ግንኙነት በመጥቀስ ከድርጊታቸው እንዲታቀቡ ማስፈራሪያ አዘል ትእዛዝ እንደሰጣቸው መረጃው አሳይቷል።

አቶ ጸጋዬ፥ እንደሳቸው ያሉ ነጋዴዎች ዋና ስጋት ከምርጫው በኋላ የንግድ ስራ እንዳይቋረጥ መሆኑና፤ በዚህም ምክንያት ፍላጎታቸው ወያኔ በስልጣን ላይ እንዲቆይ መሆኑን ለአዲስ ፎርቹን ጋዜጣ ገልጸዋል።

# ወደፊት መራመድ እንዴት አቃተን? ለወደፊቱስ ምን ማድረግ እንችላለን?

ዶ/ር ታደሰ ብሩ (ማርች 27 ቀን 2010 አስሎ፣ ኖርዌይ በተካሄደ ህዝባዊ ስብሰባ ላይ ያቀረቡት ጽሁፍ) **ክፍል 2 (ካለፈው የቀጠለ)**

ኤጭ "ማድረግ ያለብን በትዕግሥት መጠበቅ ብቻ ነው። አይባችን እንደሆነ ተመልሶ መምጣቱ አይቀርም" አለ። አሃ ባይጥመውም ተስማማ። ከዚህ በኋላ ለሣምንታት በጥዋት ወደ አይብ አልባው ጣቢያ ቁጥር 1 እየተመላለሱ ቁጭ ብለው መጠበቅ ጀመሩ። አይቡ ግን አልመጣም።

ከእለታቱ በአንዱ ቀን አሃ በድንገት በሳቅ ፈነዳ .... ከት ከት ......ከጣራ በላይ ሳቀ!!!

- "ምን ነካህ?" ኤጭ ጠየቀ በመገረም
- "ሞኝነቴ ... የዋህነቴ ... ደደብነቴ .... አንድን ነገር ደጋግሜ እየሠራሁ የተለየ ነገር መጠበቄ .... ንሳ! ጫማዎቼ ወየት ናቸው? መሄዴ ነው ....."
- "አብደሃል ... ወዴት ነው የምትሄደው ... ወደ ውጥንቅጡ? ... ወደ ጨለማው? ... አርፈህ ብትቀመጥ ይሻልሃል ... አይቡን አሁን ያመጡታል"
- "አያመጡትም ...አያመጡትም .... የሚመጣ አይብ የለም ... ያ የትናንት አይብ ነበር ... የትናንት አይብ ለዛሬ አይሆንም። የዛሬ አይብ እዚህ ጣቢያ ውስጥ አይገኝም" ይህን እየተናገረም በግድግዳው ላይ የአይብ ስዕል ስሎ **ካልተለወጥክ ትጠፋለህ!** የሚል ቃል በጉልህ ፊደላት ፃፈ።

አሃ ጫማዎቹን ተጫምቶ መንገድ ሊጀምር ሲል ኤጭ "በውጥንቅጡ ውስጥ ብትጠፋስ? አንዳችም አይብ ባታገኝስ ..." ሲለው ፍርሃት ሰውነቱን ሲወረው ተሰማው።

"ምን እንደሚገጥመኝ አላውቅም! ግን እዚህ ከመኅለት በአይብ ፍለጋ መሞት አይሻልም?" የኤጭን ምላሽ አልጠበቀም። በሃሳቡ ሰለቀረፀው ውቡ የአይብ ክምር ማሰላሰል ጀመረ። ክምሩን ሲያገኝ የሚሰማው ደስታ ታየው። ቀጥሎም ሌላ የአይብ ስዕል ሳለና **ባትፈራ ኖሮ አሁን ምን ታደርግ ነበር?** ሲል ፃፈ። ፍርሃት አንዳንዴ ጥሩ እንደሆነ ያውቃል ግና እጅና እግርን አስሮ አንዳች ነገር ከማድረግ ሲያግድ ግን ፍርሃት ክፉ ነው። "እውን ፈሪ ባልሆን ኖሮ አሁን ምን አደርግ ነበር?" ሲል ራሱን ጠየቀ። ፊቱን ከዚህ በፊት ፈጽሞ ሂዶበት ወደማያውቀው አቅጣጫ አዞረ። ፍርሃት ሆዱ ውስጥ ዘልቆ ይሰማዋል። ሆኖም ጨክኖ ገባበት!!!

ለካስ ውጥንቅጡ ሲገባበት ከሩቅ እንደሚያስፈራው አይደለም። እየተጓዘ፣ ግራና ቀኙን እየቃኘ ያስባል። አሁን አንዳንድ ነገሮች ግልጽ እየሆኑለት መጡ። አይቡ ዝም ብሎ አልጠፋም - ተበልቶ አለቀ እንጂ። "ወይኔ ሞኙ!! እንዴት ይህንን በጊዜ ይህንን ማስተዋል አቃተኝ? ...." አሃ ራሱን ወቀሰ።

አሁን ፍርሃት የሚባል ነገር ከውስጡ ጠፍቷል። በምትኩ ፍጹም ደስተኛ እንደሆነ ተሰማው። በአካልም በመንፈስም ተጠናክሮ ፍለጋውን ቀጠለ። እንዳሰበውም ታላቁን ጣብያ ቁጥር 5ን አገኘ!!!

ጣቢያ ቁጥር 5 ግዙፍ የአይብ ጣቢያ ነው። የቀድሞውን አምስት ጊዜ እጥፍ ይሆናል። የደስታና ስኬት ሲቃ እየተናነቀው እጣቢያው ውስጥ ገባ። ባዶ ነው። ጣቢያውን በጥንቃቄ መረመረ። ይህ ጣቢያ ከጥቂት ጊዜዓት በፊት በአይብ የተሞላ እንደነበረ አወቀ። ትርፍራፊዎቹን ቀመሳቸው። አቤት መጣፈጥ!!! ትንሽ ቀደም ብሎ ደርሶ ቢሆን ኖሮ ይህን የመሰለ አይብ ሊበላ ይችል እንደነበር ሲያስብ በጣቢያ ቁጥር 1 ያሳለፈው ጊዜ ቆጨው። ለመታሰቢያ ይሆን ዘንድም **አሮጌውን አይብ በቶሎ መላቀቅ፤ አዲሱን አይብ በጊዜ ያስገኛል!** ሲል ፃፈ። የጣቢያ ቁጥር 5 ባዶ መሆን በጠፋው ጊዜ እንዲቆጭ አደረገው እንጂ ተስፋ አላስቆረጠውም። እንዲያውም ሌላ የአይብ ጣቢያ ሊገኝ እንደሚችል፤ ከቀድሞው የተሻለ ጥራት ያለው አይብ ስለመኖሩም ማረጋገጫ ሆነለት። በእነዚህ ማስረጃዎች ኤጭንም ማሳመን እንደሚችል አምኖ ወደ ጣቢያ ቁጥር 1 ተመለሰ።

ኤጭ በጣቢያ ቁጥር 1 አንዷት ጥግ ተኮራምቶ በድሮው አይብ ትዝታ ሲቆዝም አገኘው። አሃ ገድሉን ባጭሩ ተረከለት። ከያዛቸውም ጣፋጭና አዳዲስ አይቦች በዓይነት ደረደረለት። ኤጭ ግን ሊያያቸው እንኳን አልፈቀደም።

"አልፈልግም። እኔ የራሴን፣ የድሮውን፣ የለመድኩትን አይብ ብቻ ነው የምፈልገው። አይቤን የምቀይርበት አንዳችም ምክንያት የለም" ኤጭ ተነጫነጨ።

አሃ እያዘነ ወደ ውጥንቅጡ ተመለሰ። አሁን አይብ ፍለጋ አንዳችም አስፈሪ ነገር የለውም። እንዲያውም አስደሳችና አዝናኝ ተግባር ሆኖለታል። "ግን ለምንድነው እንደዚህ ደስ ያለኝ? አይብ እንደሆን ገና አላገኘሁም?" በመገረም ራሱን ጠየቀ:: ቆም ብሎም **መፍራት ስታቆም ደስተኛ ትሆናለህ!!!** ፃፈ። በቅርቡ ስለሚያገኘው ውብና ጣፋጭ አይብ ሲያሰላስል ደስታው ጨመረለት። አሃ የገዛ ራሱ መቀየር ገረመው። በአዲስ አሃነቱ በደስታ እየተፍነከነከ ባለበት ሰዓት ቀድሞ ያላስተዋላቸው ቁርጭራጭ አይቦችን አስተዋለ። የአይብ ተራራ በመፈለግ ላይ ተጠምዶ ትናንሾቹን አላያቸው ኖሯል! ቁርጭራጮቹን እያነሳ በላ። የጊዜ ጉዳይ ነው እንጂ አዲስ የአይብ ጣቢያ እንደሚያገኝ ሙሉ እምነት አደረበት። እዚህ ላይ ቆም ብሎ ለብዙ ጊዜ በአዕምሮው ሲጉላላ የቆየውን አቢይ ትምህርት በግድግዳ ላይ ፃፈ።

**ትናንሽ ለውጦችን በጊዜ ማስተዋል እየመጡ ላሉ ትላልቅ ለውጦች እንድንዘጋጅ ያደርገናል።**

በበለጠ ጥንካሬና ፍጥነት ፍለጋውን ቀጠለ። ፍለጋው በራሱ አስደሳች ነው። ጥረቱን እያሻሻለ፣ ጉራንጉሮችን ሳይቀር ፈተሸ። እናም ጣቢያ ቁጥር 10ን አገኘ!!!!

ጣቢያ ቁጥር 10 ውስጥ ሲገባ ያየውን ማመን አቃተው። ይህ ያህል የአይብ ክምር ሊኖር ይችላል ብሎ መገመት እንኳን ያዳግታል። ደግሞ የዓይነቱ ብዛት!!! ይህ ነገር እውነት ነው? ዞሮ መረመረው። ቆነጣጥሮ ቀማመሰ። እፁብ ድንቅ!!!

ዞር ሲል ፈታሹና ፈጣኑ "እንኳን ደህና መጣህ" እያሉት ነው። ወዛዝተዋል። ጫማዎቹን አውጥቶ አጠገቡ አኖራቸው - ያስፍልጉት ይሆናል። ፈታሹና ፈጣኑ በአሃ መምጣት ተደስተዋል። እንደቀድሞው ጫማዎቹን በመወርወር ፋንታ አጠገቡ ሲያኖራቸው የበለጠ ደስ አላቸው። ከምርጥ የአይብ ዓይነቶች አምጥተው "እድሜ ለለውጥ!!!" እያሉ ተቋደሱ።

አሃ አካሉን ቢያሳርፍም አዕምሮው ግን አላርፍ አለው። "በምንድነው ፈታሹና ፈጣኑ የበለጡኝ?" ጥያቄውንም እራሱ መለሰው "ፈታሹ በየእለቱ ክምራችን እያነፈነፈ ትናንሽ ለውጦችን ይከታተል ነበር፤ ክምሩንም በየእለቱ ይለካ ነበርና አንድ ቀን አይባችን ማለቁ አይቀሬ መሆኑን ያውቅ ነበር። ጣቢያ ቁጥር 1 መለቀቅ ያለበት ወቅት ላይ ሲደረስ ፈጣኑ አላቅማማም.... ተያይዘው ነጎዱ። እኔና ኤጭ ግን ምን እንደተፈጠረም አልገባንም። በንትርክ ጊዜዓችንን ጨረስን፤ አይብ በማያስገኝ ሥራ ጉልበታችንን አባከንን..." ቀጥሎም ራሱን ጠየቀ "መቼ ነው እኔ የተቀየርኩት?" በጥልቀት አሰላስሎም "አንዳች የረባ ነገር ሳልሰራ ለውጥ የመጠበቄ ሞኝነት ያሳቀኝ እለት ነው እኔ የተቀየርኩት" ሲል ደመደመ። ከሁሉም በላይ ጠቃሚ ትምህርት ያለው ግን ሁሌም የተሻለ አይብ ያለ መሆኑን ማወቁ ነው።

አሁን ከቀድሞው በአስር ጊዜ የበለጠ የአይብ ክምር አለ። ቢሆንም ግን ከትንሽ እፎይታ በኋላ ጫማውን አጥልቆ ሌላ ጣቢያ ፍለጋ ተነሳ።

## ክቡራትና ክቡራን!

እንዳላሰለቸኋችሁ ተስፋ አደርጋለሁ። እስቲ ለአፍታ ራሳችን እንመርምር? አምባገነናዊ ሥልጣን፣ ሥር የሰደደ የአስተዳደር ብሉሽነት፣ ኢፍትሃዊነት፣ ችጋር ከአገራችን እንዲወገዱ እንፈልጋለን፤ ፍትህ የሰፈነባት፣ የሰዎች ነፃነት የተረጋገጠባት እና ዜጎቿ በእኩል የሚተዳደሩባት ኢትዮጵያ እንድትኖረን እንጥራለን የምንል ሁሉ ራሳችን እንጠይቅ። በትረካው ውስጥ ካሉ አራቱ ባህሪያት ማንን እንመስላለን?

ፈታሹ መምሰል ማለት አርቆ አሳቢ፣ አስተዋይ፣ አመዛዛኝ መሆን ማለት ነው (the thinker)። ፈጣኑን መምሰል የተግባር ሰው መሆን ማለት ነው (the doer)። አሃን መምሰል ማለት ብዙ ጉድለቶች ቢኖሩትም ቢያንስ ከሁኔታዎችና ከልምድ መማር የሚችል መሆን ማለት ነው። ኤጭ መሆን ማለት ደግሞ ቁጭ ብለው ሌሎቹን እየተቹና እያብጠለጠሉ "ቀን እስኪያልፍ" የሚጠብቁ ድኩማንን መሆን ማለት ነው? እስከዚችኛዋ ቀን ድረስ ማንን እንደነበርን ራሳችንን እንጠይቅ። ይህንን ጥያቄ በቅንነትና በግልጽነት ከመለስን ከዚህ አዳራሽ ሳንወጣ በአዎንታዊ ለውጥ ሂደት ውስጥ እንሆናለን።

እስቲ ደግሞ የለውጥ ኃይል ነው የሚባለውን የማኅበረሰባችንን ክፍል አስተውሉት። ማን ይበዛበታል? ክብራትና ክቡራን! በኤጮች የተገነባ ማኅበረሰብ እንደምን ነፃነቱን ሊያስከብር ይቻለዋል?

እንደሚታወቀው በዘመነ ኢንፎሜሽንና ግሎባላይዜሽን ዓለም ዓቀፍ ሁኔታዎች በፍጥነት እየተቀያየሩ ነው። የትናቱ ውሳኔያችን ለዛሬ አይሰራ ይሆናል። ትናንት ያራቅነውን ዛሬ መወዳጀት ይኖርብን ይሆናል። ለዚህ የሚረዱን ምን ያህል ፈታሾችና ፈጣኖች አሉን? ፈታሾችና ፈጣኖች ባይኖሩን እንኳን ስንቶቻችን እንደ አሃ ጊዜ ወስደንም እንኳም ቢሆን መማር ችለናል? ስንቶቻችን ፍርሃትን አሸንፈናል? ስንቶቻችንስ ከድክመቶታችንና ከውድቀቶቻችን ተምረን አዲስ አይብ፣ አዲስቷን ኢትዮጵያ ፍለጋ ተሰማርተናል?

ክቡራትና ክቡራን ወደ ዋነኛው ጥያቄዬ ልመልሳችሁ። ለምንድነው ወደፊት መራመድ ያልቻልነው?

1. እንደ ፈታሹ ትናንሽ ምልክቶችን በጥንቃቄ ተከታትለው ሊመጣ የሚችለውን እድልም ሆነ አደጋ የሚያመላክቱን በቂ ልባም ሰዎችን አላፈራንም። የነበሩን ጥቂቶችም አልተሰሙም። የኃይለሥላሴ መንግሥት አደጋ ላይ መሆኑ በርካታ ምልክቶች ነበሩ። ብዙ ባይሆኑም ጥቂት ምሁራን ምልክቶቹን አንብበው ደፍረው መክረዋቸዋል፤ አልሰሟቸውም። የሳቸው አለመስማት በራሳቸውና በቤተሰቦቻቸው ላይ ብቻ ሳይሆን በኢትዮጵያ ላይ ያደረሰውን ኪሳራ የምናውቀው ነው። የመንግሥቱም መንግሥት የውድቀት ምልክቶች እጥረት አልነበረበትም። አሁንም ጥቂት ብልህና ደፋሮች ምልክቶቹን አንብበው ለመምከር ሞከሩ፤ አልሰማቸውም። የመንግሥቱ ድንቁርና መለስ ላይ ጣለን። የመለስ መንግሥት የውድቀት ምልክቶች መታየት ከጀመሩ ቆይቷል። ጥቂቶችም ቢሆኑም ምልክቶቹን አንብበው ምክር ለመለገስ የጣሩ ነበሩ፤ አሉምም። መለስ ግን ምክሮችን ከመስማት መካሪዎቹን መግደል ይቀለዋል። ከመለስ በኋላ ምንድነው የሚመጣው? እስካሁን እኛ ራሳችን እድሎችን ልንፈጥር ይቅርና የተፈጠሩ እድሎችን እንኳን መጠቀም አልቻልንም። እንደ ማኅበረሰብ የልባሞች እጥረት አለብን። ያሉንን ጥቂት ልባሞችን ያለመስማት ደግሞ ተጨማሪ ችግር አለብን።

(ክፍል 3 ሳምንት ይቀጥላል)

## የኮንዶሚኒየም ቤቶች ተጠቃሚ ለመሆን የወያኔ አባልነት እንደሚያስፈልግ ታወቀ

በአዲስ አበባ ከተማ የኮንዶሚኒየም ቤቶች ተጠቃሚ ለመሆን እጣ ወጥቶላቸው የነበሩ ነዋሪዎች በእጣቸው መሰረት ቤቶቹ ሊሰጡዋቸው ባለመቻላቸው እያማረሩ መሆኑ ታውቋል።

4000 የሚሆኑ ቤቶች እጣ ለወጣላቸው እድለኞች መሰጠት ሲገባቸው እስካሁን አለመሰጠታቸውን፤ በሌላ በኩል ግን የገዢው ፓርቲ አባላት ለሆኑት እየተሰጡ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል። የአዲስ አበባው ዘጋቢያችን አጠናቅሮ የላከልን ዜና እንደሚገልጸው የኮንዶሚኒየም ቤት እጣ ደርሷቸው ቤቶቹን ግን ያልተረከቡት ነዋሪዎች ቤቶቹ ለምን እንደማይሰጡዋቸው ጥያቄ ሲያቀርቡ ምላሽ አለማግኘታቸውን፤ ነገር ግን የአምባገነኑ አገዛዝ ካድሬዎች የወያኔ አባል እንዲሆኑ እንደሚጎተጉቷቸው ለማወቅ ተችሏል።

ካድሬዎቹ፥ ቤቶቹ የተዘጋጁት በማህበረሰቡ ውስጥ ለወያኔ ቅስቀሳን ለማድረግ ፈቃደኛ ለሆኑ አዳዲስ የፓርቲ አባላት ነው በማለት ለእጣ አሸናፊዎቹ መናገራቸውም ታውቋል። በአሁኑ ሰአት በኢትዮጵያ ውስጥ ከገጠር እስከ ከተማ ያሉ ዜጎች ብዙ የመንግስት አገልግሎቶችን የፓርቲ አባል ካልሆኑ ለማግኘት እንደማይችሉ ሲዘገብ ቆይቷል።

## አልማ ለገቢ ማሰባሰቢያ ያዘጋጃቸው ቲኬቶች ሊሸጡ ባለመቻላቸው የአገዛዙ ካድሬዎች የቲኬቶቹን ዋጋ ለመሸፈን መገደዳቸው ታወቀ

የአማራ ልማት ማህበር (ወይም አልማ) ብሎ እራሱን የሚጠራው ድርጅት የገቢ ማሰባሰቢያ በሚል ሽፋን ያዘጋጀው ሎተሪ ተሸጦ ማለቅ ባለመቻሉ የመንግስት ሰራተኞች ድጋሚ ትኬት እንዲገዙ በአገዛዙ ካድሬዎች ጫና እየተደረገባቸው መሆኑ የታወቀ ሲሆን፣ "አንዴ ተገደን ገዝተናል፤ ሁለተኛ አንገደድም" በሚል ጫናውን መቃወማቸው ተገልጿል። አንዳንድ ሰራተኞችም የእጣ መውጫ ጊዜው በተደጋጋሚ መራዘም ግራ እንዳጋባቸው ለዘጋቢያችን አስታውቀዋል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ፥ ሽያጩን እንዲያከናውኑ ግዳጅ ተሰጥቷቸው የነበሩት የወያኔ ካድሬዎች፣ ሊሸጡ ያልቻሏቸውን ቲኬቶች ዋጋ ራሳቸው ለመሸፈን መገደዳቸውን ለማወቅ ችለናል። በጉዳዩ ላይ አስተያየት የጠየቅናቸው ግለሰብ፥ በውዴታም ሆነ በግዴታ የወያኔ ካድሬ የሆኑ ግለሰቦች እንኳ የሚኖሩበትን አይነት ፍርሃት የሚያሳይ ነው ብለዋል።

## የአምባገነን መለስ ዜናዊ አገዛዝ በመንግስት ሰራተኞች ላይ የሚያደርገውን ጫና እንደቀጠለበት ነው

የኢትዮጵያ መንግስት ሰራተኞች በወያኔ ካድሬዎች መንገላታታቸው እንደቀጠለ የግንቦት 7 ድምጽ ሪፖርተር ከአዲስ አበባ ባስተላለፈው ዘገባ አስታውቋል።

ዘጋቢያችን በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች የሚገኙ መንግስት ሰራተኞችን አነጋግሮ ባጠናከረው መረጃ መሰረት የአገዛዙ ካድሬዎች እስካሁን የአባልነት ፎርም ያልሞሉትን እየተዘዋወሩ በማፈላለግ ጫና እንደሚያደርጉባቸው ለመረዳት ችሏል። በተጨማሪም፥ ሰራተኞቹ በመጪው የምርጫ ተውኔት ማንን እንደሚመርጡ እንደሚጠየቁና፤ አልናገር ያሉትን, ካድሬዎቹ ስማቸው እንደሚጻፍ እየነገሩ እንደሚያስፈራሯቸው ታውቋል።

በዚህ ጉዳይ ላይ ስሞታቸውን ለዘጋቢያችን ያቀረቡ መንግስት ሰራተኞችም፤ ምንም እንኳ የመለስ ዜናዊን አገዛዝ እጅጉን ቢጠሉም፣ ካድሬዎቹ ዞር እንዲሉላቸው ብቻ ሲሉ ወያኔን እንደሚመርጡ እንደነገሯቸው አሳውቀውታል።

የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በምርጫ 97 በህዝብ መተፋቱ ለአለም ህዝብ ከታየ በኋላ፣ ከዛ በኋላ የህዝብ ፍላጎት እንዳይገለጽ በርትቶ እየሰራ መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን፤ ይህንን ለማድረግ ከሚጠቀማቸው ስልቶች አንዱም የመንግስት ሰራተኞችን አባል እንዲሆኑ እና እንዲመርጡት ማስገደድ እንደሆነ በሰፊው ሲዘገብ ቆይቷል።

ሂውማን ራይትስ ዋች የተባለው አለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ድርጅት በቅርቡ ባወጣው ሪፖርት ላይ፣ መንግስት ሰራተኞችን ጨምሮ በርካታ ምንጮችን በመጥቀስ, ከ1997 ወዲህ የመንግስት ሰራተኛው የፓርቲ አባል እንዲሆን እና የወያኔን ፖሊሲ እንዲቀበል የተለያዩ ጫናዎች እየተደረጉበት መሆኑን ገልጿል።

## መጋቢ ዳንኤል ገብረስላሴ እስረኞችን በመርዳት ስም በወሰደው ገንዘብ ለወያኔ ባለስልጣናት ስጦታ ገዝቶ ማደሉ ተደረሰበት

የቤተክርስቲያን አገልጋይ እንደሆነ የሚናገረው እና በፕሮፌሰር ኤፍሬም ይስሃቅ የሚመራው የሽማግሌዎች ቡድን አባል የሆነው መጋቢ ዳንኤል ገብረስላሴ በእስረኞች ስም የተቀበለውን ገንዘብ ለወያኔ ባለስልጣናት ስጦታን ገዝቶ ከማደል ጀምሮ ላልታቀደባቸው ሌሎች ተግባራት ማዋሉን ለግንቦት 7 ድምጽ ሬድዮ የደረሰ መረጃ አሳይቷል።

ግለሰቡ ከአምባገነን መለስ ዜናዊ አገዛዝ ጋር የሙስና ትስስር እንዳለው ከዚህ ቀደም መዘገባችን ይታወሳል። ሐሙስ፣ መጋቢት 30፣ 2002 አመተ ምህረት ባስተላለፍነው ዜና፣ መጋቢ ዳንኤል በከፍተኛ ሙስና ውስጥ ስለመዘፈቁ ጥርጣሬዎች ስለበረከቱ ለሚመራው ግብረ ሰናይ ድርጅት የገንዘብ ድጋፍ ያደርጉ ከነበሩት አለም አቀፍ ለጋሽ ቡድኖች ውስጥ የተወሰኑት በድርጅቱ ላይ ኦዲት ወይም የሂሳብ ማወራረድ ስራ እንዲደረጉ እና ያም ከፍተኛ ገንዘብ መመዝበሩን እንዳጋለጠ መዘገባችን ይታወሳል።

በዚህ ሳምንት በጉዳዩ ላይ የደረሰን ተጨማሪ መረጃ፥ የሂሳብ ማወራረድ ስራው ካጋለጣቸው ተግባሮች ውስጥ አንዱ መጋቢ ዳንኤል ለሌላ ስራ የተቀበለውን ገንዘብ ተጠቅሞ በርካታ ኮምፒውተሮችን በመግዛት ለወያኔ ባለ ስልጣናት እንዳደለ ያሳያል። ይህንን ለምን እንዳደረገ የተጠየቀው ዳንኤል፣ የቅንጅት መሪዎችን ለማስፈታት በተደረገው ሽምግልና ወቅት ለስራዬ እንዲረዳኝ ብዬ ነው ቢልም፤ ለጋሾቹ ገንዘቡን የሰጡት ለዛ ጉዳይ እንዳልሆነ ሲያስታውሱት የሚመልሰው እንዳልነበረው የግንቦት 7 ድምጽ ምንጮች ገልጸዋል።

በጉዳዩ ላይ መረጃ የላኩልን ምንጮች፥ ገንዘቡ ላልተሰጠበት ስራ መዋሉ አንድ ራሱን የቻለ ጉዳይ ሆኖ ሳለ፤ ለወያኔ ባለስልጣናት ኮምፒውተር ገዝቶ ማደሉ እንዴት አድርጎ የሽምግልናውን ስራ ሊረዳ እንደሚችል ግልጽ አይደለም ሲሉ አስተያየታቸውን አካተዋል። "ጀስቲስ ፎር ኦል" የሚባለው የመጋቢ ዳንኤል ድርጅት ሌሎች መንግስታዊ ድርጅቶችን በር ያስዘጋው የመያዶች ህግ እንደማይመለከተው እና ከአምባገነን መለዝ ዜናዊ አፋኝ የደህንነት ሃይሎች ጋር በሽርክና እንደሚሰራ ከዚህ ቀደም ባስተላለፍነው ዜና መዘገባችን ይታወሳል።

መጋቢ ዳንኤል የቅንጅት መሪዎችን ለማስፈታት በተደረግው ሽምግልና ስም ሌላም ገንዘብ እንዳጠፋ የታወቀ ሲሆን፤ ፕሮፌሰር ኤፍሬም ይስሃቅ ከአሜሪካን አገር ለዛ ጉዳይ ወደ ኢትዮጵያ እየተመላለሱ በሸራተን ሆቴል ሲያርፉ የሳቸውን ሂሳብ የሚሸፍነው የመጋቢ ዳንኤል ድርጅት እንደነበረና ይህም ከለጋሾች የተገኘ ገንዘብ ለዛ ጉዳይ የተሰጠው እንዳልነበረ ምንጮቻችን ገልጸዋል።

በተጨማሪም፥ ይሄው አይሪሽ ኤድ በተባለውና የአየርላንድ መንግስት እርዳታ ሰጪ በሆነው ግብረ ሰናይ ድርጅት መሪነት የተካሄደው የሂሳብ ማወራረድ ስራ፣ መጋቢ ዳንኤል ገብረስላሴ ለአንድ ስራው ከአይሪሽ ኤድ እና ከዩስ ኤድ ድርጅቶች እጥፍ ደሞዝ ሲቀበል መቆየቱን አጋልጧል።

## አርሶ አደሮች ወያኔ የግብርና ልማት . . . ከገጽ 1 የዞረ

ወያኔ አለኝ የሚላቸውን 4 ሚሊዮን አባላት በተመለከተ ደግሞ፣ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዜጎች ስራቸውን ወይም ከመንግስት መስሪያ ቤቶች የሚገኙ አገልግሎቶችን እንዳያጡ ሰግተው የአባልነት ቅጽ ሲሞሉ መቆየታቸው በተለያዩ የዜና አውታሮች በሰፊው መዘገቡ ይታወቃል።

ሂውማን ራይትስ ዋች የተባለው አለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ተከራካሪ ድርጅት በቅርቡ ላወጣው ሪፖርት ቃሉን የሰጠ አንድ የሲዳማ ዞን አርሶ አደር ለምን የወያኔ አባል እንደሆነ ሲገልጽ እንዲህ ብሏል፥ "እኔ የኢህአዴግ አባል ነኝ፤ ነገር ግን የምደግፈው ተቃዋሚዎችን ነው። የኢህአዴግ አባል መሆን ማለት ምንም ማለት አይደለም። እኔ አባል የሆንኩበት ምክንያት እርዳታ ለማግኘት ነው። እርዳታ ለማግኘት፥ ለፓርቲው መዋጮ የተከፈለበትን ደረሰኝ ማሳየት ያስፈልጋል። መዋጮ የምከፍለውም መጨቆን እና መዘንጋት ስለማልፈልግ ነው።"

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**
**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**
**በ 7140፣ 7175፣ 7185 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ እና በ 6100 KHZ በ 49 ሜትር ባንድ**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ፣ ሐሙስ እና ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት እስከ 3፡30፤ እንዲሁም ከምሽቱ 2 ሰዓት እስከ 2፡30 የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።